# የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን
# በኦታዋ
# መተዳደሪያ ደንብ

June 2006

## ማውጫ

# ቅጽ ፩ አባልነት

ክፍል 1-1 አባል የመሆን መንገድ
ክፍል 1-2 የአባልነት መብትና ኃላፊነት
ክፍል 1-3 የአባላት ልጆች
ክፍል 1-4 ከአባልነት መሰናበት
ክፍል 1-5 የአባላት መዝገብ
ክፍል 1-6 የሥነ ሥርአት እርምጃ በአባላት ላይ የሚወሰድባቸው ምክንያቶች
ክፍል 1-7 በሥነ ሥርአት እርምጃ በኩል የሚደረግ ተኀድሶ

# ቅጽ ፪ የአመራር ክፍሎች

ክፍል 2-1 የቤተ ክርስትያን የሽማግሌዎች ቦርድ
ክፍል 2-2 ዲያቆናት
ክፍል 2-3 የበላይ ጠባቂ ቦርድ
ክፍል 2-4 የሂሳብ ሹም

# ቅጽ ፫ ተቀጣሪ ሠራተኞች/ሙሉ ጊዜ አገልጋዮች

ክፍል 3-1 እረኛ

# ቅጽ ፬ ስብሰባዎች

ክፍል 5-1 ቋሚ ስብሰባዎች

# ቅጽ ፭ የሂሳብ ክፍል

ክፍል 5-1፦ የሂሳብ መመሪያና አላማ

# ቅጽ ፮ ሥርአቶችና ልምምዶች

ክፍል 6-1 ሥርአቶች
ክፍል 6-2 ልምምዶች፡
ክፍል 6-3፦ የክህነት ሥርአት

# ቅጽ ፯ እርማት

ክፍል 7-1፦ አሠራር
ክፍል 7-2፦ የእምነት አንቀጽ እርማት

## ቃላትና ፍቺ

መመዘኛ፡- አንድ ግለሰብ ወደ አባልነት በተለይም ወደ ቤተ ክርስትያን አገልግሎት ከመሰማራቱ በፊት ለተጠራበት አገልግሎት ኃላፊነት ብቁ መሆኑን የሚገልጡ በጽሑፍ የሰፈሩ መመሪያዎች

መብት፡- እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ ቤተ ክርስትያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ ራሳቸውን ለቤተ ክርስትያን የሰጡ ግለሰቦች እንደ እግዚአብሄር ቃልና መተዳደሪያው ደንቡ እንደሚያሳየው ከቤተ ክርስትያን የሚጠብቁትና ከቤተ ክርስትያኒቱ የሚደረግላቸው ማንኛውም አገልግሎት።

ማስታወቂያ፡- መሪዎች በቤተ ክርስትያን የሚደረገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ለአባላትና ለምእመናን በጽሑፍ ሆነ በቃል ቤተ ክርስትያኒቱ ባላት የአምልኮና አጠቃላይ የአባላት ስበሰባ የሚያስተላልፉት ኢንፎርሜሽን።

ሥልጣን፡- መሪዎች በእግዚአብሔርና በሚመሩት ህዝብ ፊት ብቃታቸው ታምኖበት፣ ለመምራት የሚያስችላቸውን ሙሉ ነጻነት ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስትያን የሚቀበሉት ኃላፊነት ነው። ሥልጣን ሰጪ ይሰጣል ሥልጣን ተቀባይ ይቀበላል እንጂ ሥልጣንን ማንም ለራሱ ሊወስድ አይችልም።

ራእይ፡- በሩቅ ወይም በቅርብ ያለ፣ ወደፊት ሊደረስበት የሚችል ነገር ግን ዛሬ ላይ ተቁሞ የሚታይና በሥርአት የተነደፈ እቅድ።

ሰነድ ማንኛውም በወረቀት ላይ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ የተያዘ ህጋዊ የሆን ወይም ያልሆነ መረጃ

ሽማግሌ፡- በሽማግሌ ቦርድ ውስጥ እንዲያገለግል በጠቅላላ የአባላት ጉባኤ የመተመረጠ ከመንፈሳዊ መሪዎች አንዱ

ቃለ መጠይቅ፡- የሽማግሌዎች ቦርድ ሙሉ ጊዜ አገልጋይን ለመጥራት ሆነ የቤተ ክርስትያንን የቢሮ ስራ ለማከናወን የሚቀጥሯቸውን ቅጥር ሠራተኞችን ከመቅጠራቸው በፊት ለመመዘኛ እንዲሆን በሽማግሌዎች ጉባኤ ከእጩ ቅጥረኞች ጋር የሚደረግ ጥያቄና መልስ።

ቃለ ጉባኤ፡- በማንኛውም የጠቅላላ አባላት ስብሰባ ጊዜና በማናቸውም በቤተክርስትያኒቱ ውስጥ ባሉት የቦርዶች ስብሰባ ላይ ተመዝግቦ የሚያዝ የውይይት ውሳኔ።

ባጀት፡- በጽሑፍ የቀረበ የቤተ ክርስትያኒቱን ወርሀዊ ወይም ዓመታዊ የገንዘብ ወጪ ተመንና ገንዘቡ የሚወጣበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰነድ።

ቦርድ፡- በቤተ ክርስትያኒቱ ውስጥ የአመራሩን ስልጣን የተቀበሉ መማክርትን ያቀፉ የአመራር ክፍሎች። ለምሳሌ የሽማግሌዎች ቦርድ፣ የዲያቆናት ቦርድ . . .ወዘተ።

አባል፡- በክፍል 1-2 እንደተጠቀሰው ሙሉ አባል፣ ጽምጽ የመስጠት ሙሉ መብት ያለው፣ በማንኛውም መመዘኛዎችን በሚያሚላበት የአመራርና የአገልግሎት ክፍሎች በመሳተፍ ለማገልገል፣ ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ ሙሉ መብት ያለው።

አናሳ ጉሩፕ፡- ቁጥራቸው ከ12 በታች የሆነ ትናንሽ ስብስብ። በክፍል 5-1-2-ለ እንደተጠቀሰው ለመንፈሳዊ እድገት ምክንያት እንዲሆንና የአገልግሎት ክፍሎችን ለማደራጀት ቤተ ክርስትያኒቱ የምታደራ

ጃቸውን የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናት፣ የሴቶች ኮሚቴንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

ቤተ ክርስትያን፦ የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ በመባል የምትታወቅን የቅዱሳን ህብረት ሲያሳይ ይህም ህብረት ሕጋዊ ህልውና ያለው የወንጌልን ሥራ የሚሠራ የቤተ ክርስትያን ህብረት ነው።

እጅ መጫን፦ መሪዎችን ለመሾምና ስልጣንን ለማስተላለፍ የሚደረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርአት

እጩ መጋቢ/እጩ አረኛ፦ የመጋቢነቱን ኃላፊነት ያልተቀበለ ነገር ግን በሽማግሌዎች ቦርድ ውስጥ ገብቶ ለማገልገልና የመጋቢነትን ኃላፊነት ከእግዚአብሔር፣ ከሽማግሌዎችና ከጉባኤው ተቀብሎ ለመሥራት በሽማግሌዎች ተመርጠው ለአጠቃላይ ጉባኤ ምርጫ ከሚቀርቡት እጩ መጋቢዎች ወይም አረኞች አንዱ።

ክህነት፦ ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎችና ዲያቆናት ሌሎችም መንፈሳዊ መሪዎች በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ጉባኤ ፊት እጅ በመጫን ሥርአት የሚቀበሉት መንፈሳዊ ኃላፊነት

ኮረም፦ በአንድ ስብሰባ ላይ ለውሳኔ የሚያበቃ የስብሰባው ተካፋዮች ብዛት በቁጥር

ዋስትና፦ ቁዋሚ ለሆነ ንብረት በጥፋት ጊዜ ለመተካት የሚያስችል ከሌላ ድርጅት ጋር የሚደረስ ስምምነት

የቤተ ክርስትያን መተዳደሪያ ደንብ፦ ይህ በቤተ ክርስትያኒቱ የጠቅላላ አባላት ጉባኤ የጸደቀ የቤተ ክርስትያኒቱን አላማና መዋቅር የሚያሳይ በጽሑፍ የቀረበ መመሪያ

የሚሽን ሥራ፦ በቅርብም ሆነ በቅርብ ላሉት በሥጋም ሆነ በመንፈሳዊ ነገር ተግባራዊ ድጋፍ በመስጠት በቤተ ክርስትያኒቱ የሚሠራ መንፈሳዊ አገልግሎት

የበላይ ጠባቂዎች፦ የቤተ ክርስትያኒቱን አጠቃላይ ንብረት በኃላፊነት ተቀብለው በተገቢው መንገድ በበላይነት የሚጠብቁና የሚያስተዳድሩ

የእምነት አንቀጽ፦ በጽሑፍ የቀረበ መሠረታዊውን የቤተ ክርስትያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እምነት።

የደቀ መዝሙር ቃል ኪዳን/ የአባልነት ቃል ኪዳን፦ የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ አባል ለመሆን የወሰኑ የሚገቡት ቃል ኪዳን

የፓርላማ ስብሰባ ሥርአት፦ በመሪዎችና በአባላት ስብሰባ ጊዜ መሪዎች ሊከተሉት የሚገባ ፍሬአማ የሆነ ስብሰባን የመምራት ስርአት ሲሆን “Robert’s Rules of Order” በመባል ይታወቃል።

ጠቅላላ ጉባኤ፦ በአባላት ስብሰባ ላይ ከ3/4 በላይ የተገኘ የአባላት ጉባኤ።

## ቅጽ ፩ አባልነት

አንድ ሰው የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ አባል ለመሆን በሚወስንበት ጊዜ የሚከተሉትን አባል የመሆኛ መንገዶች መከተል ይገባዋል።

ክፍል 1-1 አባል የመሆን መንገድ

1. አባል የመሆን ጥያቄ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል።

2. አባል የመሆን ጥያቄ ላቀረቡ ግለሰቦች የቤተ ክርስትያኒቱ መሠረታዊ የእምነት አንቀጽና የመተዳደሪያ ደንብ ሙሉ እትም ይሰጣቸዋል። ለአባልነት ጥያቄ ያቀረቡት ግለሰቦች የተቀበሉትን የእምነት አንቀጽና መተዳደሪያ ደንብ በሙሉ ማንበብ ይጠበቅባቸዋል።

3. አባል ለመሆን ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦች ለአዲስ አባላት የተዘጋጀውን፤ መሠረታዊውን የቤተ ክርስትያን የእምነት አንቀጽና የመተዳደሪያ ደንቡን ያጠቃለለ፣ እንዲሁም የአባልነትን ኃላፊነት በሚመለከት የሚ ቀርበውን ትምህርት መካፈል ይጠበቅባቸዋል።

4. አባል ለመሆን ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦች በቤተ ክርስትያኒቱ የተዘጋጀውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳ ኝነትና ጌታ መሆን የሚገልጹበትን እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንቡ ለተገለጸው ለቤተ ክርስትያኒቱ ሥል ጣን ለመገዛት ራሳቸውን መስጠታቸውን የሚያሳዩበትን የአባልነት ቅጽ ይሞላሉ።

5. ለአባልነት ጥያቄ ያቀረቡ ማናቸውም ግለሰቦች የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ የምትከተለውን መሠረታዊውን የእምነት ትምህርት መረዳታቸውንና የአባልነትን ቃል ኪዳን ለመግባት መወሰናቸውን በምስክርነት ቃላቸው ማሳወቅ አለባቸው። ምስክርነታቸውንም በቤተ ክርስትያን የሽማግሌዎች ቦርድ ፊት፣ በሽማግሌዎች ቦርድ በተወከሉ የቦርዱ አባላት ፊት ማስተላለፍ ይችላሉ። ከዚህ በኋላ የሽማግሌ ዎች ቦርድ አባል ለመሆን ጥያቄ ያቀረቡትን ግለሰቦች በመገምገም አጥጋቢ ሆኖ ካገኙት ግለሰቦቹ በቀ ጥታ የቤተ ክርስትያኒቱ አባላት ይሆናሉ።

6. የሽማግሌዎች ቦርድ ለአባልነት ጥያቄ ያቀረቡትን ግለሰቦች ለአባልነት ከተቀበሉ በኋላ ቤተ ክርስትያኒ ቱ ባላት የእሁድ የአምልኮ ፕሮግራም በቤተ ክርስትያኒቱ አጠቃላይ ጉባኤ ፊት ወደ አባልነት መጨመ ራቸውን በመንገር ጉባኤው እንዲቀበላቸው ይደረጋል። አዲስ አባላት በፈቃዳቸው በጉባኤው ፊት ምስ ክርነታቸውን እንዲሰጡ እድል ይሰጣቸዋል።

ክፍል 1-2 የአባልነት መብትና ኃላፊነት

የቤተ ክርስትያን አባል የሚከተሉትን ተግባራት፣ እድሎችና መብቶችን ይቀበላል፦

1. እንደ ክርስቶስ አካል አንዱ የአንዱን መንፈሳዊ ፍላጎት በማገልገል አብሮ የማደግ እድል።

2. ጌታ እንደመራ፣ እንደተቀበልነው ጸጋ መጠንና እንደ መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በተለያዩ የቤተ ክርስ ትያኒቱ አገልግሎቶች በመሳተፍ የመሥራት እድል።

3. እግዚአብሔር እንደመራ የቤተ ክርስትያኒቱን ሥራ በገንዘብ የመርዳት ተግባር (በመባና በአሥራት)።

4. በመተዳደሪያ ደንቡ እንደተገለጸው ለቤተ ክርስትያኒቱ ሥልጣንና ሥርአት መገዛትና የቤተ ክርስትያኒቱ ን ሥልጣንና ሥርአት የማክበር ተግባር።

5. ቤተ ክርስትያኒቱ ለሕዝብ ሁሉ በምታዘጋጀው መንፈሳዊ ፕሮግራሞች በመገኘት የመካፈል እድል።

6. ቤተ ክርስትያኒቱ በምታዘጋጀው ቅዱስ ሥርአት የመካፈል እድል (የጌታ እራት፣ የጥምቀት ሥርአት)።

7. በአባላት ስብሰባ ሁሉ የመገኘትና ድምጽ የመስጠት መብት።

8. በማንኛውም አባላትን በሚመለከት ምርጫ ላይ በመገኘት የመምረጥ መብት። በምርጫው ላይ በበቂ ም ክንያት መገኘት ያልቻለ አባል ካለ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በቁጥር ከሁለት በላይ ሆነው ወደ ግለ ሰቡ በመሄድ ድምጽ እንዲሰጥ ማስደረግ አለባቸው።

9. የድምጽ መስጠት መብትን በውክልና መፈጸም አይቻልም።

10. አባላት በቤተ ክርስትያኗ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱ የተለያዩ ኃላፊነቶችን የመቀበል ኃላፊነትና በመሠረታዊው የእምነት አንቀጽ መሠረት በመኖር የሚገቡትን የአባልነት ቃል ኪዳን በሕይ ወታቸው የመጠበቅ ኃላፊነት።

<u>ክፍል 1-3 የአባላት ልጆች</u>

የቤተ ክርስትያን አባላት ልጆች በመወለድ ብቻ የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ አባላት አይሆኑ ም፤ ወይም እድሜአቸው ለአባልነት ሲደርስ የአባላት ልጆች ስለሆኑ በቀጥታ አባል መሆን አይችሉም። ማንኛውም እድሜው ለአባልነት የደረሰ ግለሰብ የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን አባል ለመሆን፣ ጌታ ኢየ ሱስ ክርስቶስን በማመን ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት የጀመረ ሊሆን ይገባል። ይህ ግንኙነት በግ ል ኢየሱስን በማመን እንጂ በትውልድ ወይም በውርስ የሚገኝ አይደለም። የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያ ን ወጣቶች የአባልነትን እድልና መብት እንዳይካፈሉ የማድረግ ምንም አይነት እቅድ የላትም። ስለዚህ ወጣቶች በእድሜ 14 ዓመት ካለፉና ከሽማግሌዎች ቦርድ ጋር በመገናኘት የቤተ ክርስትያኒቱን መሠረታ ዊ እምነትና የአባልነትን ቃል ኪዳን መረዳታቸውን ከመሰከሩ የቤተ ክርስትያን አባል መሆን ይችላሉ። የሽማግሌዎች ቦርድም እድሜአቸው 14ና ከ14 በላይ የሆኑትን ወጣቶች በመከታተል የቤተ ክርስትያን አባልነት ፍላጎታቸውን የማጠናከርና የማበረታታት ኃላፊነት አለባቸው።

<u>ክፍል 1-4 ከአባልነት መሰናበት</u>

ከአባልነት መሰናበት ወይም መወገድ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሊፈጸም ይችላል።

1. <u>በዝውውር</u>፦ በመልካም ምስክርነት የቆዩ አባላት የሌላ ቤተ ክርስትያን አባል ለመሆን ወይም ሥፍ ራና አገር ለቀው በሚሄዱበት ሰዓት ከቤተ ክርስትያን የሽኝት ደብዳቤ ከጠየቁ በቤተ ክርስትያን የሽማግሌዎች ቦርድ ስምምነት ደብዳቤ ከቤተ ክርስትያን ይሰጣቸዋል።

2. <u>በግል ጥያቄ</u>፦ አንድ አባል በራሱ ፈቃድ፣ በማንኛውም ምክንያት የቤተ ክርስትያን አባልነቱ እንዲ ሰረዝ ከጠየቀ ጥያቄው ይፈጸምለታል። የአባልነት መቋረጥ ጥያቄውን ባቀረበው አባ ልና በቤተ ክርስትያን መካከል ያልተፈታ ችግር ቢኖር ከአባልነት የመሰረዝ ጥያቄው ን ከመመለሳቸው በፊት የሽማግሌዎች ቦርድ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለ

በት። የአባልነት መቋረጥ ጥያቄ ያቀረቡት ግለሰቦች በቤተ ክርስትያን ተገስጸው የሥ ነ ሥርአት እርምጃ የተወሰደባቸው ከሆኑ የተወሰደባቸውን የሥነ ሥርአት እርምጃ እስኪፈጽሙ ድረስ ለቤተ ክርስትያን ሥልጣን መገዛታቸውን በመቀጠል በአባልነት ይቆያሉ። በዚህ መንገድ ያሉ አባላት የሥነ ሥርአት እርምጃቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከአባልነት መቋረጥ ጥያቄአቸውን በማቅረብ ከአባልነት የመቋረጥ መብታቸው ይጠበ ቅላቸዋል። የአባልነት መቋረጥ ጥያቄው ቀርቦ አባልነት በሚቋረጥበት ሰዓት ጥያቄው ን ያቀረቡት አባላት በማንኛውም የቤተክርስትያኒቱ አገልግሎት ውስጥ ያላቸውን ኃላ ፊነት በማስረከብ አገልግሎታቸውን ያበቃሉ።

3. <u>በቅጣት፦</u> ማንኛውም አባል በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጥንቃቄ ሳይኖር መልካም ምስክርነትና ምሳሌነት ባጠቃላይ ቅድስና በጎደለው ሕይወት የሚመላለስ ከሆነ በማቴዎስ 18፥15-17 መሠረት የሽማግሌዎች ቦርድ የሥነ ሥርአት እርምጃ ይወስዳል። ቤተ ክርስትያኗ እርማትና ግሣ ጼ አለበለዚያም ከአባልነት የማስወገድ መብት አላት። ይህም ሊሆን የሚችለው የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ግለሰቡን ለመመለስ፣ ለማረም መልካም መንፈሳዊ ጥረት አድርገ ው ካልተቻለ በቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ስብሰባ በሙሉ ድምጽ ከተደገፈና ከአባላት 3/4 በተገኙበት ስብሰባ በድምጽ ብልጫ ውሳኔው ሲያልፍ ነው።

4. <u>በመቅረት፦</u> አንድ አባል ከቤተ ክርስትያን ያለምንም በቂ ምክንያት ከ6 ወር በላይ ከቀረ በሽማግሌ ዎች ቦርድ በኩል አባልነቱ ይሰርዛል። ነገር ግን መቅረቱ በጤና ወይንም በሌላ ችግር ለሽማግሌዎች ቦርድ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት ከሆነ ላይሰረዝ ይችላል።

5. <u>በሞት፦</u> አባላት በሞት ሲለዩ

6. ማናቸውም አባላት አባልነታቸው እንዲቋረጥ ሲፈልጉ ጥያቄውን ለሽማግሌዎች ቦርድ በጽሑፍ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ሲሆን አባልነታቸው እንዲቋረጥ የፈለጉበትንም ምክንያት በጹሑፉ ላይ እንዲገልጹ ይጠየቃሉ።

<u>ክፍል 1-5 የአባላት መዝገብ</u>

አባል የሆኑትና ከአባልነት የተሰናበቱት አባላት መዝገብ በጸሐፊው ተዘጋጅቶ ይቀመጣል።

<u>ክፍል 1-6 የሥነ ሥርአት እርምጃ በአባላት ላይ የሚወሰድባቸው ምክንያቶች</u>

የሽማግሌዎች ቦርድ አባላት በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ሲገኙ የሥነ ሥርአት እርምጃ ይወስዳሉ፦

1. ግብረገብነት የጎደለው ተግባርና ባህሪ ሲታይባቸው
2. በቤተ ክርስትያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ ላይ እንደተገለጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለሆነው ሥልጣንና ሥርአት ለመገዛት ፈቃደኛ ሆነው ካልተገኙ።
3. ከቤተ ክርስትያኒቱ የእምነት አንቀጽ ጋር የሚጻረር ሌላ ትምህርት ሲቀበልና ከቤተ ክርስትያኗ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጋር ሲቃረን።
4. አንዱ አባል ሌላውን አባል ሲጎዳው፣ መከፋፈልን በአባላት መካከል ሲያመጣ፣ ከዚህም ስህተቱ በንስሀ ካልተመለሰና ችግሮቹ ካልተፈቱ።

<u>በክፍል 1-7 በሥነ ሥርአት እርምጃ በኩል የሚደረግ ተጎድሶ</u>

1. የሽማግሌዎች ቦርድ በአባላት ላይ የሥነ ሥርአት እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነታቸውን በሚወጡበት ጊዜ ኢየሱስ አንዳችን አንዳችንን በትህትናና በፍቅር እንድንመለከትና አንዳችን የአንዳችንን ሸክም እንድንሸከም ያሳሰበንን ቃል በልባቸው ሊጠብቁት ይገባል። የሥነ ሥርአት እርምጃ የሚወሰድበት

ተቀዳሚ አላማ በማናቸውም አይነት በደል የተገኘውን ሰው በማደስ እንደገና ሕብረትን ከእግዚአብ ሔርና ከቤተ ክርስትያን ጋር እንዲያደርግ ነው። ቤተ ክርስትያን እንዲህ አይነቱን እርምጃ የመው ሰድ መብት ብቻ ሳይሆን ያላት ነገር ግን መንፈሳዊ በሆነ መንገድ ልታደርገውና ልትለማመደው ይገባል። ይህ በሚደረግበት ሰዓት የቤተ ክርስትያኒቱ አባላት ለእያንዳንዱ አባል መንፈሳዊ ሕይወት በማሰብና ለቤተ ክርስትያን ምስክርነት በማሰብ መልካም የሆነ ምሳሌነትን በውጭ ባሉት ፊት ለማሳ የት ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

2. የአባልነት መቋረጥ ከፍተኛው የሥነ ሥርአት እርምጃ ሲሆን ያሉት አማራጮች ሁሉ ከተሞከሩ በኋላ የሚወሰድ እርምጃ ይሆናል።

## ቅጽ ፪ የአመራር ክፍሎች

<u>ክፍል 2-1 የቤተ ክርስትያን የሽማግሌዎች ቦርድ</u>

1. <u>ምርጫ፦</u> ሽማግሌዎች በቤተ ክርስትያን አባላት ተጠቁመው ለሽምግልና አገልግሎት በቀረበው መመ ዘኛ መሠረት በጊዜው ባለው የሽማግሌዎች ቦርድ ተቀባይነት ካገኙ በኋላ በአጠቃላይ የአ ባላት ስብሰባ ላይ ከ3/4 በላይ አባላት በተገኙበት በድምጽ ብልጫ ይመረጣሉ። አዲስ የሽ ማግሌ ቦርድ አባል የጎደለ ቦታን ለመሙላት አለዚያም የሽማግሌ አባል ለመጨመር ከጠቅ ላላ ጉባኤው 3/4 አባላት በተገኙበት ስብሰባ ላይ ይመረጣል።

2. <u>የአገልግሎት ዘመን፦</u> የሽምግልና ቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ከተመረጡበት ጊዜ አንስቶ ሦስት (3) ዓመት ይሆናል። በተጨማሪም አንድ ሽማግሌ የአገልግሎት ዘመኑ ባበቃበት ጊዜ ሁሉ ጉባኤው እስከመረጠው ድረስ እንደገና መመረጥ ይችላል።

3. <u>የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ፦</u>

    1. ሽማግሌዎች በራሳቸው ጥያቄ ወይም ከጠቅላላ ጉባኤ ለሽማግሌዎች በተሰጠ ው ሥልጣን በኩል በጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ላይ በተገኙ አባላት 3/4 ድም ጽ የሥራ ዘመናቸው ሊያበቃ ይችላል።

    2. የግል ጉዳያቸው የሚጠበቅባቸውን ተገቢውን ጊዜና ጉልበታቸውን እንደሚገባ ለተጠሩበት አገልግሎት እንዲሰጡ የማያስችላቸው ከሆነ ከሽምግልና ቦርድ አባልነት ነጻ መሆን ይችላሉ።

    3. አንድ የሽምግልና ቦርድ አባል ከቦርድ አባልነቱ መነሳት ከፈለገ በጽሑፍ የቀ ረበ የሠላሳ ቀን ጊዜ መስጠት ይኖርበታል።

    4. የሽማግሌ ቦርድ አባል በአባላት ጥያቄ ከ3/4 በላይ አባላት በተገኙበት ስብሰባ በድምጽ ብልጫ የሥራ ዘመን ሊያበቃ ይችላል።

4. <u>መመዘኛዎች፦</u>

- በአእምሮና በመንፈሳዊው ነገር የበሰሉ።

- በመንፈሳዊ ባህሪያቸው፣ በሚሰጡት ሚዛናዊ አሳብና በኑሮአቸው በሚያሳዩት መልካም ምሳሌ ብቁ መሪዎችና አስተማሪዎች መሆናቸው የተመሰከረላቸው (ጢሞቴዎስ 3፥1-7ና ቲቶ1፥5-9 1 ጴጥሮስ 5፥1-3፣ የሐዋሪያት ሥራ 6፥4፣ ኤፌሶን 4፥11፣ ኤፌሶን 5፥21-33)

- ከቤተሰባቸው ጋር በአንድነት ቤተ ክርስትያኒቱን ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑ።

- በቤተ ክርስትያን አገልግሎት ውስጥ በትጋት የሚሳተፉና በአገልግሎታቸው የተመሰከረ ላቸው ሊሆኑ ይገባል።

- ለሽምግልና የሚመረጡት አባላት መመዘኛውን ካሟሉና እድሜአቸው ከሃያ አንድ (21) በላይ ከሆነ ወንዶች ወይም ሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

- የቤተ ክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ፣ የውስጥ ደንብና የእምነት አንቀጽ በሙሉ ልብ የተቀበሉና የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ አባል የሆኑ።

- በሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን ቢያንስ ለሁለት ዓመት አባል የነበሩና ከዚያም በፊት በነ በሩበት ቤተ ክርስትያን በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው የተመሰከረላቸው።

- አዲስ አማኞች ከሆኑ በቤተ ክርስተያኗ ውስጥ ለሦስት ዓመት የቆዩና ቤተ ክርስትያኒ ቱ ለምእመናኖቿ መንፈሳዊ እድገት በማሰብ በምታዘጋጃቸው የትምህርትና የልምምድ ፕሮጋራሞችን በመከታተል የሚተጉ ሊሆኑ ይገባል። በተጨማሪም እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን በአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ ተሰማርተው በማገልገልና በየእለት ኑሮአቸው የቤተክርስትያንን አላማ እንደተረዱ ማሳየት አለባቸው።

- ለሽምግልና አገልግሎት የሚመረጡ ለዚህ አገልግሎት መመረጣቸው ከዚህ በፊት ስላደረጉት መልካም ነገርና ስለሰጡት አገልግሎት ዋጋ እንዲሆን የተሰጣቸው የክብር ቦታ ሳይሆን በትህትናና በመስጠት ለማገልገል ራሳቸውን ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብ ሔር ሕዝብ የሚያቀርቡበት አገልግሎት ነው።

- ለዚህ አገልግሎት የሚመረጡ በሽማግሌዎች ቦርድ ውስጥ ብቻ ተወስነው የአስተዳደ ርን ሥራ እንዲሠሩ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቤተ ክርስትያን በምትፈልጋቸውና በሚ ችሉት አገልግሎት ሁሉ በመሳተፍ ለቤተ ክርስትያኒቱ እድገት የሚተጉ መሆን አለባቸ ው።

- ለቤተ ክርስትያን ሽማግሌነት የተመረጡ በጊዜው ባሉት የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች እጅ መጫን በጠቅላላ ምእመናን ፊት ለአገልግሎቱ ይካናሉ።

5. <u>የሽማግሌዎች ቦርድ አባልነትና ብዛት</u>፡- የቤተ ክርስትያን ሽማግሌ ቦርድ አባላት በቤተ ክርስትያን አጠቃላይ ጉባኤ ተጠቁመው፣ በመመዘኛው መሠረት በጊዜው ባለው የሽማግሌ ቦርድ ጸድቀው በአጠቃላይ ጉባኤው የድምጽ ብልጫ የተመረጡትን ያጠቃልላል። የሽማግሌ ቦርድ ቁጥር ከሦስት አያንስም ከሰባት አይበልጥም።

6. <u>ኃላፊነትና ሥልጣን</u> ፡- የሽማግሌ ቦርድ ለጠቅላላ መንፈሳዊና አስተዳደሪያዊ እንዲሁም ጊዜያዊ ለሆኑት የቤተክርስትያን ጉዳዮች ኃላፊ ሲሆን ከእግዚአብሔር ሥልጣን በታች ቤተ ክርስትያንን እየተቆጣጠረ ቤተ ክርስትያኒቱ በስሟ የምትሳተፍበትን ሕጋዊ የሆነ ማንኛ

ውንም ጉዳይም በበላይነት ይመለከታል፣ ይከታተላል፣ ይወስናል። በተለይም ለአባላ ትና ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት እድገት እያንዳንዳንዳቸው የሽምግልና ቦርድ አባለ ት በሚሰጣቸው ኃላፊነት መሠረትና እንደ እግዚአብሔር ቃል ተግተው የመሥራት ኃላፊነት አለባቸው።

<u>የሽማግሌዎች ቦርድ ኃላፊነትና ሥልጣን በዝርዝር፦</u>

1. የየእለቱን የቤተ ክርስትያን አስተዳደሪያዊ ሥራና ሌሎች የቤተ ክርስትያን እንቅስቃሴዎችን (ተግባራትን) በኃላፊነት መፈጸምና የቤተ ክርስትያንን የገን ዘብ ወጪ በባጀት መሠረት መውጣቱን በበላይነት መከታተል። ከመጋቢው ጋር በመሆን እቅዶችንና መመሪያዎችን መንደፍና በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በአባላት ከጸደቁ በኋላ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ።

2. መጋቢው መንፈሳዊ አመራርን ለቤተ ክርስትያን በሚሰጥበት ጊዜ ወቅታዊና አመቺ ሆኖ እንደተገኘ መጠን ራእዮቹንና ፕሮግራሞቹን በሥራ ላይ እንዲው ል ለማድረግ ከመጋቢው ጋር ተባብሮ መሥራትና የመጋቢውን መንፈሳዊ ሥል ጣን ማክበር።

3. የመጋቢውንና የጉባኤውን ግንኙነት መመርመርና ለውጥ የሚያስፈልግ ከሆነና ተገቢ ከሆነ አስፈላጊነቱ ታይቶ ለውይይትና ሀሳቡን ለማጽደቅ የአባላት ስብሰ ባ መጥራት።

4. ማንኛውንም የአባላት ስብሰባ መጥራትና የስብሰባውን ሰዓት፣ ቀንና ቦታ ለአባ ላት ማሳወቅ።

5. የቤተ ክርስትያንን መተዳደሪያ ደንብ፣ ዓላማና ራእይ መተርጎም። ይህም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ቤተ ክርስትያን የተመሰረተችበትን የመኖሯን አላማ በመፈጸም አላማዋን ለመሙላት የምትችልበትን የእድገት መንገድ ይከፍትላታል።

6. የቤተ ክርስትያን አባላት የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ አገልግሎት በመረዳ ት የቤተ ክርስትያንን አላማና ግብ በተመሳሳይ መንገድ መዘርጋት።

7. በተለያዩ የቤተ ክርስትያን ኮሚቴዎች፣ ቦርዶች፣ የአገልግሎት ክፍሎች፣ እንዲሁም ቤተ ክርስትያን ባቀረበችላቸው የአግልግሎት መጠቀሚያ ንብረቶ ች በመጠቀም ቤተ ክርስትያኒቱ ግቧን እንድትመታ በሚያገለግሉት ግለሰቦች የሚቀየሰውን የአገልግሎት መንገድና የአገልግሎቱን እድገት በበላይነት መከ ታተል። ግለሰቦችን ለተወሰነ ጊዜ በተለያዩ ቦርዶችና በሌሎችም አገልግሎቶ ች ውስጥ በመመደብ መልካም የግንኙነት መንገዶችን በሽማግሌዎች ቦርድና በተለያዩ ቦርዶች ወይም አገልግሎቶች መካከል መፍጠር።

8. የቤተ ክርስትያን አባላት ምስክርነት በጎደለው ሕይወት ሲጓዙና በስህተት መንገድ ላይ ሲገኙ የመምከርና አስፈላጊም ከሆነ በማቴዎስ 18፥15-17 መሠ ረት የሥነ ሥርአት እርምጃ መውሰድ፣

9. በክፍል 1-4 ቁጥር 3 ላይ በተጠቀሰው መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ የአባልነት መብትን መሰረዝ

10. ከአጠቃላይ ጉባኤ ለሽምግልና፣ ለዲያቆናት፣ ለበላይ ጠባቂነትና ለሂሳብ ሹም አገልግሎት ፈቃደኛ የሆኑትን ግለሰቦች ጥቆማ የመቀበል።

11. በቁጥር 5 ለተጠቀሱት አገልግሎቶች የተጠቆሙትና የጸደቁት ግለሰቦች በት ክክለኛ መንገድ በቤተ ክርስትያን አባላት መመረጣቸውን ማረጋገጥ።

12. የሽማግሌ ቦርድ አባልን፣ የዲያቆን ቦርድ አባልን ወይም የሂሳብ ሹምን ከሥ ልጣን የማንሳት መብት አላቸው። ይህንንም ሥልጣን ለመጠቀም ከ3/4 አባላ ት በላይ የተገኙበት የአጠቃላይ ጉባኤን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። የሽማግሌ ቦርድ አንድን የቦርድ አባል ከአገልግሎት ለማንሳት ሙሉ የቦርድ ድምጽ ማግኘት አለበት።

13. ተገቢውን ዓመታዊ ሪፖርት ለአባላት ማቅረብና አባላት ለሚጠይቁት ጥያቄ ተገቢውን መልስ መስጠት።

7. <u>የሽምግልና ቦርድ ስብሰባ</u>፦

1. የሽምግልና ቦርድ ስብሰባ ሲደረግ የስብሰባው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በቦርዱ እንደተወሰነ ይሆናል።

2. የቦርዱ አባላት ማናቸውም ለውይይት ወደ ቦርዱ የሚመጡትን አሳቦች በምስ ጢር የመጠበቅና ይህንንም በማድረግ ለሌሎች በቤተ ክርስትይኒቱ ላሉት ቦር ዶችና የአገልግሎት ክፍሎች እንዲሁም መሪዎች ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

<u>ክፍል 2-3 ዲያቆናት</u>

1. <u>ምርጫ</u>፦ ዲያቆናት በአጠቃላይ ጉባኤ ይጠቆማሉ። በመመዘኛው መሠረት በቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ቦርድ ከጸደቁ በኋላ በ3/4 የአጠቃላይ ጉባኤ አባላት በተገኙበት በድምጽ ብልጫ ይመረጣሉ። በዲያቆናት ቦርድ ውስጥ የጎደለን ቦታ ለመሙላት ወይም ለመጨ መር ከተፈለገ አዲስ የዲያቆን አባል ይመረጣል። ይህም በቤተ ክርስትያን የሽማግሌዎች ቦርድ ወይም በአባላት ስብሰባ በ3/4 የአጠቃላይ ጉባኤ ድምጽ ብልጫ ይፈጸማል።

2. <u>የአገልግሎት ዘመን</u>፦ የዲያቆናት ቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ከተመረጡበት ጊዜ አንስቶ ለሁ ለት (2) ዓመት ይሆናል። በተጨማሪም አንድ ዲያቆን የአገልግሎት ዘመኑ ባበቃበት ጊዜ ሁሉ ጉባኤው እስከመረጠው ድረስ እንደገና መመረጥ ይችላል።

3. <u>መመዘኛዎች</u>፦

- በክርስትና ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው፣ እርጋታና ማስተዋል የሞላባቸው፤ ለምእመ ናን በሥጦታቸው፣ ቤተ ክርስትያን በሚኖራት ፕሮግራሞች ሁሉ ላይ በመገኘት፣ በመ ንፈሳዊ ብስለታቸው፣ በቅድስና ኑሮአቸው መልካም ምሳሌ የሆኑ መሆን አለባቸው።

- በሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በአባልነት ለሁለት ዓመት የቆዩና በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ በጸጋቸው ተሰልፈው በትጋት ያገለገሉ።

- ለዚህ አገልግሎት ለምርጫ የሚቀርቡት በሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በአባልነት የቆዩ በት ጊዜ ከሁለት ዓመት ያነሰ ከሆነ አስቀድመው ከነበሩበት ቤተ ክርስትያን ስለ መን ፈሳዊ ሕይወታቸው ምስክርነት ከተገኘ በኋላ ለምርጫው መቅረብ ይችላሉ።

- ለዚህ አገልግሎት የሚመረጡት በሐዋሪያት ሥራ 6፥3ና በጢሞቴዎስ 3፥8-13 የተጠቀ ሰውን መመዘኛ ሊያሟሉ ይገባል።

- ለዚህ አገልግሎት የቀረበውን መመዘኛ እስካሟሉ ድረስ ወንዶች ወይም ሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

- የምርጫው ሥርአት አብቅቶ የተመረጡት ዲያቆናት በሽማግሌዎች እጅ መጫን ለድ ቁና አገልግሎት በጠቅላላ ምእመናን ፊት የክህነት ሥርዓት ከተደረገላቸው በኋላ የዲ ያቆንነት አገልግሎትን ይረከባሉ።

4. <u>አባልነትና ብዛት፡-</u> ይህ ቦርድ በአጠቃላይ ጉባኤ ተጠቁመው በሽማግሌ ቦርድ ከጸደቁ በኋላ አባላት በጠቅላላ የአባላት ስብሰባ በድምጽ ብልጫ ያሳለፏቸውን ያቀፈ ቦርድ ነው። የዲያቆናት ቦርድ ቁጥር ከሦስት አያንስም ከሰባት አይበልጥም።

5. <u>ኃላፊነት፡-</u> ይህ ቦርድ የሽማግሌዎችን ቦርድ ጊዜያዊ በሆኑ የተለያዩ የቤተ ክርስትያን አገልግሎቶችን እያገዘ ይሠራል። በተለይ፡-

   1. ለምዕመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማለትም በእምነታቸው፣ በጸሎት፣ በቤተሰባቸው መካከል በሚታይ መንፈሳዊ እድገትና ወንጌልን ለማወጅ ባላቸው ቅንአትና ድፍረት መልካም የመሪነት ምሳሌ በማሳየት።

   2. የታመሙ ወገኖችን፣ አዛውንትን፣ የታሰሩ ቢኖሩ እንዲሁም ሌሎች መጎብኘት የሚገባቸውን ሁሉ በመጎብኘት።

   3. የምዕመናን በአጠቃላይ የኮሚኒቲውን ያልተሟላ ሥጋዊ ፍላጎት በመረዳት መፍትሄ ሊያስገኙ የሚችሉ መንገዶችን መፈለግ።

   4. ከእርዳታ መዋጮ ገንዘብ ወጭ በማድረግ በመጽሐፍ ቅዱስና በዲያቆን ቦርድ መመሪያ መሠረት ማከፋፈል።

   5. ሥርዓት የያዘና አጥጋቢ የሆነ መንገድ በመፈለግ በቤተ ክርስትያን የተሰበ ሰቡትን ገንዘቦችና ሥጦታዎችን መቁጠርና በባንክ ማስገባት።

   6. እንደ አስፈላጊነቱ በቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሥርዓት ላይ አገልግሎት መስ ጠት።

   7. የቤተ ክርስትያንን ምዕመናን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የሂሳብ አጠቃቀም ስልትን፣ አያያዝና አሰጣጥን በማወቅ እንዲያድጉና ክርስትያናዊ የሆነ የገ ንዘብ ነጻነት እንዲኖራቸው መርዳት።

6. <u>ቅንጅትና ሥርአት፡-</u> የዲያቆናት ቦርድ አሠራር ሥርአት በቦርዱ ይወሰናል። ሰብሳቢው በቦርዱ ይመረጣል። ሰብሳቢው ስብሰባ በመጥራትና ስብሰባውን በመምራት እንዲሁም ቦርዱን በመወከል ለጠቅላላው ጉባኤ የቦርዱ ቃል ሰጪ በመሆን ያገለግላል።

የዲያቆናት ቦርድ ተጠያቂነቱ ለሽማግሌዎች ቦርድና ለቤተ ክርስትያን ጠቅላላ ጉባኤ ነው። የዲያቆናት ቦርድን ለማቋቋም የማይቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር የዚህ ቦርድ አገልግሎት በሽማግሌዎች ይፈጸማል።

7. ስብሰባ፡- የዲያቆናት ቦርድ አስፈላጊ በሆነበት ሰዓት ስብሰባቸውን ያካሂዳሉ። ሰብሳቢው አባላቱን በ ግል በመገናኘት ስብሰባውን ይጠራል። ውሳኔ ለመስጠት 3/4 አባላት መገኘት አለባቸው

8. ሥልጣን፡- የዲያቆናት ቦርድ የተቀበሉትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችላቸው በተመደበላቸው ባጀት መሠረት ገንዘብን የመጠቀም መብት አላቸው።

## ክፍል 2-3 የበላይ ጠባቂ ቦርድ

1. ምርጫ፡- ለበላይ ጠባቂነት የሚመረጡ አባላት የሚጠቆሙት ከቤተ ክርስትያን ጉባኤ ሲሆን በሽማግሌዎች ቦርድ ከጸደቁ በኋላ በአባላት ስብሰባ ላይ በ3/4 የአጠቃላይ ጉባኤ አባላት በተገኙበት ድምጽ ብልጫ ለበላይ ጠባቂነት አገልግሎት ይመረጣሉ።

2. የአገልግሎት ዘመን፡- የበላይ ጠባቂ አባላት የአገልግሎት ዘመን ከተመረጡበት ጊዜ አንስቶ ለሦስት (3) ዓመት ይሆናል። በተጨማሪም የበላይ ጠባቂ የአገልግሎት ዘመኑ ባበቃበት ጊዜ ሁሉ ጉባኤው እስከመረጠው ድረስ እንደገና መመረጥ ይችላል።

3. የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ፡- የበላይ ጠባቂ አባላት በራሳቸው ፈቃድ ወይም በ3/4 የአጠቃላይ ጉባኤ ድምጽ ከሥራቸው ሊሰናበቱ ይችላሉ።

4. መመዘኛዎች፡- የበላይ ጠባቂ አባላት የቤተ ክርስትያን አባላት ሆነው ስለተመረጡበት አገልግሎት በቂ መረዳት ያላቸውና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉ ሊሆኑ ይገባል። በተጨማሪም ለዚህ አገልግሎት የሚመረጡት ንብረትን በማስተዳደር፣ ሕግንና የዋስትናን አሠራር እውቀትና ልምድ ያላቸው፣ ወይም ጠቅለል ያለ የአስተዳደር ልምድ ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል።

5. አባልና ብዛት፡- ይህ ቦርድ ቢያንስ ሦስት አባላት ሊኖሩት ይገባል። እነዚህም አባላት በጉባኤ ተጠቁመው በሽማግሌ ቦርድ ጸድቀው በአባላት ድምጽ ብልጫ የተመረጡ ይሆናሉ።

6. ኃላፊነት፡- በአጠቃላይ የማይንቀሳቀስ ቋሚ የቤተ ክርስትያን ንብረትን መቆጣጠር፣ መጠበቅና በሥርአት መያዝን ያጠቃልላል። በዚህም ውስጥ የቤተ ክርስትያን ንብረትን አጠቃቀም ይመለከታል። ይህም በቤተ ክርስትያን ንብረት ውስጥ ዋጋቸው ከ $100.00 በላይ የሆኑትን በሙሉ ማለትም መሬት፣ ሕንጻ፣ የሙዚቃ መሣሪያ እንዲሁም ሌሎችን ሁሉ ያጠቃልላል። የበላይ ጠባቂ ቦርድ ማንኛውም ሕግን የሚመለከትን ነገር ሁሉ ይሳተፋል። በተለይ፡-

   - አጠቃላይ ጉባኤን በመወከል የመግዛት፣ የመሸጥ፣ ኮንትራት የመያዝ ወይም መከራየትን ይከታተላል። በውሳኔም ላይ ይገኛል፣ ድምጽ ይሰጣል።
   - የቤተ ክርስትያን ንብረቶችን አያያዝ በቅርብ በመከታተል፣ አስፈላጊ ከሆነም ሌላ በመወከል እድሳትን ያደርጋል፣ ለውጥ ለሚያስፈልጋቸውም ለውጥ ያደርጋል።
   - ለቤተ ክርስትያን ንብረት በቂ ዋስትና እንዲኖር ያደርጋል።

- ለቤተ ክርስትያን ሽማግሌ ቦርድ የወደፊት የንብረት ወጪዎችን በሚመለከት አሳቦችን ያቀርባል።

7. <u>ቅንብርና ሥርአት፦</u> ይህ ቦርድ የራሱን የመሰብሰቢያ ጊዜን፣ ሰብሳቢን ይመርጣል። ሰብሳቢው ቦርዱን በሽማግሌዎች ቦርድ ይወክላል። ለአጠቃላይ ጉባኤም ቃል ሰጪ ይሆናል። ይህ ቦርድ ለሽማግሌዎች ቦርድና ለአጠቃላይ ጉባኤ ተጠያቂ ነው።

<u>ክፍል 2-4 የሂሳብ ሹም</u>

1. <u>ምርጫ፦</u> የሂሳብ ሹም አገልግሎት በነጻ የሚሰጥ አገልግሎት ነው። በቤተ ክርስትያን ሽማግሌ ጸድቆ በአባላት ስብሰባ በ3/4 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በተገኙበት በድምጽ ብልጫ ምርጫው ይደረጋል።

2. <u>የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ፦</u> የሂሳብ ሹም አገልግሎቱን በራሱ ፈቃድ፣ በሽማግሌዎች ቦርድ እርምጃ ወይም በአባላት ስብሰባ በ3/4 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በተገኙበት በድምጽ ብልጫ ከአገልግሎቱ ሊሰናበት ይችላል።

3. <u>መመዘኛ፦</u> የሂሳብ ሹም ሙሉ የቤተ ክርስትያን አባል መሆን አለበት። በተጨማሪም የተሰጠውን አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ሊያሠራ የሚችል፣ በቂ የሆነ የሂሳብ አሠራር እውቀት ሊኖረ ው ይገባል። ሁኔታዎች እንደፈቀዱ የሂሳብ ሹሙ የዲያቆናት ቦርድ አባል ቢሆን ይመ ረጣል። የሐዋሪያት ሥራ 6፣1-6 እንደተጠቀሰው ከመጀመሪያው የቤተ ክርስትያን አስተ ዳደርና የገንዘብ አያያዝ ለዲያቆናት የተሰጠ አገልግሎት ነው።

4. <u>ኃላፊነት፦</u> የሂሳብ ሹም ኃላፊነት

   ሀ. የቤተ ክርስትያኒቱን አጠቃላይ ገንዘብ በተገቢው የባንክ ሂሳብ መያዝና በእምነት መጠበቅ።

   ለ. የቤተክርስትያኗን የገንዘብ ወጪና ገቢ በተገቢ ሥርአት መያዝና ማካሄድ

   ሐ. የቤተ ክርስትያኗን የሦስት ወር የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለአባላት ማሰራጨት። እንዲሁ ም የዓመቱን አጠቃላይ የሂሳብ ሪፖርትና መግለጫ ማዘጋጀትና ለአጠቃላይ ጉባኤ ማቅረብ

5. <u>ተጠያቂነት፦</u> በአጠቃላይ የሂሳብ ክፍል ሹም ለቤተ ክርስትያን አጠቃላይ ጉባኤ ተጠያቂነት ሲኖ ረው በበለጠ ደግሞ ለቤተ ክርስትያን የሽማግሌዎች ቦርድ ተጠያቂ ነው። (መልስ የ መስጠት ኃላፊነት አለበት)

6. የሂሳብ ሹም በማይኖርበት ጊዜ ሥራው በሽማግሌዎች ቦርድ በተመረጠ አባል እንዲሸፈን ይደረጋል

## ቅጽ ፫ ተቀጣሪ ሠራተኞች/የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች

<u>ክፍል 3-1 እረኛ፦</u>

<u>1. አመራረጥ</u>

1. <u>የእረኛ አስመራጭ ኮሚቴ</u>

   ሀ. <u>አመሠራረት፦</u> ይህ ኮሚቴ ከሦስት ያላነሱ ፈቃደኛ የሆኑ የሽማግሌ ቦርድ አባላትና

ሁለት በአጠቃላይ ጉባኤ የተመረጡ አባላት ይኖሩበታል።

ለ. <u>ኃላፊነት</u>፦ በአጠቃላይ ለእረኝነት የቀረቡ አባላትን (ግለሰብን) መምረጥና ለቤተ ክርስትያን አጠቃላይ ጉባኤ ማዘጋጀት ሲሆን ይህንንም ለማድረግ፦

- መመዘኛ ነጥቦችን ማዘጋጀት
- አገልጋዮችን መፈለግና ማነጋገር
- የተመራጭ አባላትን የትምህርትና አገልግሎት ጊዚያትን መመርመርና ማጥናት
- ተመራጮች በቤተ ክርስትያን ጊዜና ቦታ አግኝተው የሚሰ ሙበትን (በጉባኤ) መድረክ ማዘጋጀት
- የድምጽ አሰጣጥና አመራረጡን ሥርዓት ማዘጋጀት

በተቻለ መጠን የመጋቢ (እረኛ) አስመራጭ ኮሚቴ ጥሪ ያለውን ሰው ለማግኘት አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ቢያደርግ ይመረጣል። ይህ ኮሚቴ ከሌሎች መጋቢዎችና ሽማግሌዎች ጋር በመገናኘት የእጩ እረኛን ተግባ ርና መንፈሳዊ ነገሮችን ይመረምራል።

ሐ. <u>ሥልጣን</u>፦ ይህ ኮሚቴ በቤተ ክርስትያን በተመደበለት ባጀት መሠረት ይህንን አገልግሎት ለማካሄድ ወጪን ማድረግ፣ ማስፈቀድ ይችላል።

መ. <u>ለምርጫ ብቁነት</u>፦ እጩ እረኞች በቤተ ክርስትያን ጉባኤ መልእክት እንዲያቀርቡ ተደረጎ ከዚያም ከአስመራጭ ኮሚቴው ጋር ከተገናኙና ማጠቃለ ያ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው በኋላ ይህ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ ብቁ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን እጩ መጋቢዎች ለድምጽ ብልጫ ምርጫ ለቤተ ክርስትያን ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል። መጋቢ በአጠ ቃላይ የአባላት ስብሰባ በ3/4 የጉባኤ ድምጽ ብልጫ ይመረጣል።

ሠ. <u>የአገልግሎት ዘመን</u>፦ አንድ እረኛ ላልተወሰነ ጊዜ ይሾማል። የአገልግሎት ጊዜው በራሱ በእረኛው ጥያቄ፣ በሞት ወይም በአጠቃላይ የአባላት ስብሰባ በ3/4 የ ጉባኤ ድምጽ ብልጫ ሊቋረጥ ወይም ሊሰናበት ይችላል። አንድ እረኛ በፈቃ ደኝነት ከተሰናበተ ለቤተ ክርስትያን የ30 ቀናት የመዘጋጃ ጊዜ መስጠት አለበ ት። ቤተ ክርስትያንም አንድ እረኛ ካሰናበተች የ30 ቀን የዝግጅት ጊዜ አለበ ለዚያም የ30 ቀን ደመወዝ መስጠት አለባት።

2. <u>የአቀጣጠር ሁኔታዎች</u>፦ የእረኛው ደመወዝና ቋሚ የሆኑ ወጪዎች (የቤት ወጪ፣ ዋስትና፣ ጡረታና ሌሎች ወጪዎች) የስምምነቱ ሰነድ ክፍል ሆነው በትክክል በጽሑ ፍ ተዘጋጅተው በአጠቃላይ ጉባኤ ድምጽ ይሰጥባቸዋል። እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች፣ ለስብሰባ ጉዞ ወጪ፣ ዝውውር ጊዜ የሚወጣ ወጪ፣ የዓመት እ ረፍት ወጪና ሌላም ተጨማሪ ነገሮች በስምምነት ሰነድ ላይ መታየት አለባ ቸው።
ሰነዱ ሕጋዊ የሆነ የስምምነት ፊርማ ያለበት ጽሑፍ ነው። የአቀጣጠር ሁኔ ታዎችን ለመለወጥ ሙሉ ሥልጣን የአጠቃላይ ጉባኤ ድምጽ ብቻ ነው።

3. መመዘኛዎች፦ የእረኛ መመዘኛው በ 1 ጢሞቴዎስ 3፥1-7፣ በቲቶ 1፥6-9ና 1 ጴጥሮስ 5፥ 1-3 ላይ በተጠቀሰው በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ መሠረት ይሆናል። ከዚህ በተረፈ በእረኛ አስ መራጭ ኮሚቴ የሚቀርቡትን ጠቅላላ መመዘኛዎች ማሟላት ይገባዋል። ከዚህ በኋ

ላ በሽማግሌዎች እጅ መጫን የእረኝነቱ ሽክምና ሥልጣን ይሰጠዋል።

4. *ኃላፊነትና ሥልጣን* ፦ እረኛው የቤተ ክርስትያኒቱን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በበላይነት በመመልከት ተቀዳሚ ሲሆን ተግባሩና ያለው ሥልጣን እንደሚከተለው ነው፦

- ለቤተ ክርስትያን መንፈሳዊ ምሪትን የመስጠት ተግባርና መንፈሳዊ አመራርን ተግባ ራዊ ለማድረግ ከሽማግሌዎች ቦርድ ጋር አብሮ የመሥራት ኃላፊነት
- በየጊዜው አስፈላጊ ሆኖ እንደተገኘ ከሽምግልና ቦርድ ጋር አብሮ መመሪያዎችንና ሕጎችን በማውጣትና ሀሳብ በመስጠት ተግባር ላይ መገኘት
- ጉባኤውን በማስተማር፣ በመስበክና በማሠልጠን ማገልገል
- ቀን በቀን የሚፈጸሙ የቤተ ክርስትያን አገልግሎቶችን መፈጸምና ለምክር በተፈለገ ሰዓት መገኘት
- መጎብኘት የሚገባቸውን ምዕመናንን በቤታቸው መጎብኘት
- የቤተ ክርስትያንን ሥርአትና አገልግሎት መፈጸምና ማስፈጸም
- ተቀጣሪ ሠራተኞችን መቆጣጠርና አስፈላጊውን ፈቃድ የመስጠት፣ በሽምግልና ቦርድ ከጸደቀም መቅጠርና ከሥራ የማሰናበት ኃላፊነት
- በ 1 ጢሞቴዎስ 3፥ 1-7፣ ቲቶ 1፥5-9ና 1 ጴጥሮስ 5፥ 1-3 የተጠቀሱትን መመዘኛ ዎች የማሟላት ኃላፊነትና በሕይወቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር የተጋጨ ግብረ ገባዊነት ከጎደለውና ቅድስና ከጎደለው ባህሪ የመራቅ ኃላፊነት።
- ለቤተ ክርስትያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ የመገዛት ኃላፊነትና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ እንደተጠቀሰው ከቤተ ክርስትያን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ጋር ተስማ ምቶ የመኀዝ ኃላፊነት። በዚሁም ከማንኛውም አከራካሪ ከሆኑ ትምህርቶችና ል ምምዶች ራሱን የመጠበቅ ኃላፊነት። መጋቢው የቤተ ክርስትያንን ትምህርት ሳይ ጠብቅ የሚጓዝ ከሆን የሽምግልና ቦርዱ አስፈላጊውን ምክርና እርምጃ ይወስዳል።

5. *የውጪ አገልግሎቶች*፦ ማንኛቸውም እረኛው ከቤተ ክርስትያን ውጪ የሚሳተፍባቸውን አገልግሎቶች ለሽማግሌዎች ቦርድ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

6. *ሥልጣንና ገደብ*፦ እረኛው የገንዘብ ወጪዎችን በማዘዝ ላይ እንደ ሽማግሌ ቦርድ አባልነቱ የተወሰነ ነው። እንዲሁም እረኛው ከቤተ ክርስትያኒቱ ትምህርት ወይም በእምነት አንቀጽ ላይ ከተጠቀሱት መሠረታዊ እምነት ጋር ሳይቃረን የእግዚአብ ሔርን ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) በማስተማር ምዕመናንን የማገልገል ሙሉ ሥልጣን አለው።

## ቅጽ ፬ ስብሰባዎች

**<u>ክፍል 4-1 ቋሚ ስብሰባዎች</u>**

1. <u>የእሁድ አምልኮ</u>፦ የእሁድ አምልኮ ምእመናን በቤተ ክርስትያን ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ

በት፣ በእግዚአብሔር ቃል የሚታነጹበትና፣ በመንፈስ አንድነት ውስጥ ሆነው አን ዱ ሌላውን የሚያገለግልበት ጊዜ ነው። የዚህ ስብሰባ ኃላፊነት በቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ላይ የተጣለ ሲሆን በተለይ ግን እረኛው ይህንን የማደራጀት ሙሉ ኃላፊነትና ሥልጣን አለው።

2. <u>ሌሎች የአገልግሎት ክፍሎች</u>፦ እነኚህ የተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎችን የያዙና የሚመሩ በሳምንቱ ውስጥ ከእሁድ አገልግሎት ሌላ በቤትም ሆነ በቤተ ክርስትያን የሚገናኙ የቤተ ክርስትያን አገልግሎት ክፍሎችን ያጠቃልላል።

   ሀ. <u>የአገልግሎት ክፍሎች አወቃቀር</u>፦ የቤተ ክርስትያኒቷ አባላት በሙሉ ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉት ጸጋ መጠን ባሉት የተለያዩ የአገልግሎት ክፍ ሎች ውስጥ በመግባት እንዲሳተፉ ጥረት መደረግ አለበት። የአገልግሎት ክ ፍሎች አወቃቀር የቤተ ክርስትያኒቱ መጋቢ ባለው መንፈሳዊ ራእይ መሠረት ከሽማግሌዎች ቦርድ ጋር በመማከር የሚፈጸም ይሆናል።

   ለ. <u>የአገልግሎት ክፍሎች አስፈላጊነት</u>፦ በተቻለ መጠን በሐዋሪያት ዘመን በነበረው አይነት ልምምድ በአናሳ ግሩፕ በመደራጀት በቤት ውስጥ የሚደረግ የክርስት ያኖች ህብረት (የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ግሩፕ፣ የሴቶች ህብረት፣) ለመፍጠር ና በዚህም ውስጥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱትን አንዳንድ መንፈሳዊ መመሪያዎችን ለመጠቀምና ለመለማመድ የሚያስችል መንገድን ለማመቻቸት ይጠቅማል። ከነዚህምውስጥ፦

      - በእያንዳንዳችን የግል ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የሚሠራው ን ትርጉም ያለውን ሥራውን ለማየትና በዚህም እርሱን በማወቅ ለማደግ።
      - የእግዚአብሔርን ቃል ከቀን ወደ ቀን ከየእለት ኑሮአችን ጋር በማዛመድ ለማጥናት (ቆላስይስ 3፥16፣ 2ጢሞቴዎስ 3፥16)።
      - እርስ በርስ እውነትን በፍቅር እየተነጋገርን በንስሃና ድካማችንን በመከፋፈል አንዳችን የአንዳችንን ሸክም በጸሎት በመሸከም፣ እንዲሁም እርስ በርስ በመጽናናት፥እርስ በርስ በመበረታታትና ቁሳዊ ነገሮችንም በመካፈል እንድንበረታ (ገላትያ 6፥2፣ ያዕቆብ 5፥16፣ ተሰሎንቄ 4፥18፣ ዕብራውያን 3፥13፣ የሐዋርያት ሥራ 4፥32፣ ያዕቆብ 5፥16፣ ኤፌሶን 4፥ 15፣25)።
      - እርስ በእርስ ለአገልግሎት በመነሣሣት አንዱ ሌላው ያለውን የጸጋ ሥጦታ በማየትና በመደገፍ የራሱንም መንፈሳዊ ሥጦታ ለይቶ በማወቅ ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲዘጋጅ ለማበረታታት (ኤፌሶን 4፥12፣ 1ጴጥሮስ 4፥10-11)
      - ከቤተ ክርስትያን ውጭ ላሉት ለመመስከር እርስ በርስ ለመበረ ታታት (ማቴዎስ 28፥18-20፣ዮሐንስ 17፥21)

   ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ሌላ የአገልግሎት ክፍል አባላትና በአናሳ ጉሩፕ ያሉ ት አባላት በሌሎች በተለያዩ አገልግሎት ክፍሎችና አናሳ ጉሩፖች መሳተፍ ይችላሉ። ይህም ማለት እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል ወይም አናሳ ጉሩፕ ባለው ፈቃድና በጊዜው በሚኖረው መንፈሳዊ ፍላጎት መሠረት የሽማግሌዎች

ቦርድ ይህንን ለማሟላት አስፈላጊውን አገልግሎቶችን በማደራጀት ይሠራል። ይህም ማለት ለምሳሌ የሂሳብ አያያዝ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስን በቃል ለማ ስታወስ ለመርዳት፣ ከቤተክርስትያን ውጭ ያሉትን ለመድረስ በምስክርነት አገልግሎት የሚደረግ የወንጌል ሥራና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

ሐ. <u>የአገልግሎት ክፍሎች ስብሰባ</u>፦ አብዛኛውን ጊዜ የአገልግሎት ክፍሎች በሳምንት አንድ ቀን ስብሰባ ያደርጋሉ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የአገልግሎቱ ክፍል አባላት እንደተስማሙ የስብሰባውን ቀን ይጨምራሉ ወይም ይቀንሳሉ። የስ ብሰባው ቦታና ሰዓት እንደአስፈላጊነቱ ለምዕመናን ከስብሰባው ሳምንት በፊ ት ባለው እሁድ ይገለጻል።

3. የአባላት ስብሰባ ፦ ይህ ስብሰባ የቤተ ክርስትያንን ሥራ በተመለከተ የሚደረግ አጠቃላይ የአባላት ስብሰባ ነው።

ሀ. <u>የስብሰባው ማስታወቂያ</u>፦ ማንኛውም አጠቃላይ የአባላት ስብሰባ ሲኖር ቢያንስ ከሁለ ት ሳምንት በፊት ለእያንዳንዱ አባል የስብሰባ ጥሪ በጽሑፍ መቅረብ አለበት ። በቤተ ክርስትያን ቡለትን ላይ ከስብሰባው ቀን በፊት በሁለት እሁዶች እን ዲጻፍ፣ አለበለዚያም ከስብሰባው በፊት በሁለት እሁዶች ላይ የስብሰባው ቦታ ና ሰዓት በማስታወቂያ መነገር አለበት። እንደ አስፈላጊነቱ የስብሰባው ጉዳይ ታይቶ የሁለት ሳምንት የማስታወቂያ ጊዜ ሊያጥር ይችላል። ይህም በሽማግሌ ዎች ቦርድ ውሳኔ ይሆናል።

ለ. <u>የስብሰባው መሪ</u>፦ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ቦርድ መሪ እንደ ስብሰባው መሪ ሆኖ ሊመራ ከፈለገም ሌላ የሽማግሌ አባል መተካት ይችላል።

ሐ. <u>ኮረም</u>፦ በአባላት ስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት ለዚያን ዕለት ስብሰባ በቂ ድምጽ ይኖራቸ ዋል። ነገር ግን የአባላት ስብሰባው የቤተ ክርስትያኗን የአቋም ለውጥ፣ የእ ምነት አንቀጽ፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የመሸጥ የመግዛት፤ ለረዥም ዘመን የመከራየት ወይም ሞርጌጅን እንዲሁም የስምምነት ሰነድና እረኛን የመምረጥ ወይም የማሰናበት፣ ሌሎችን የቤተ ክርስትያን ተቀጣሪዎችን የማሰናበት አጀን ዳ ከሆነ ኮረሙ ቢያንስ 3/4 የቤተ ክርስትያን አባላትን መያዝ አለበት።

መ. <u>የስብሰባው ሥርአት</u>፦ ማንኛውም የአባላት ስብሰባ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት ውስጥ አብዛኛውን ድምጽ ማግኘት አለበት። ድምጽ መስጠት የሚችሉት የቤ ተ ክርስትያን አባላት ብቻ ናቸው። የሽማግሌ ቦርድ በድምጽ ብልጫ ያለፈን ነገር ውሳኔውን ሊያስለውጡ የሚችሉ በቂ ምክንያቶች ካሉ እንደገና አባላት እንዲመለከቱትና ድምጽ እንዲሰጡበት የመጠየቅ መብትና ሥልጣን አላቸው። ይህም ሥርአት ከአንድ ጊዜ በላይ አይደረግም።

ሠ. <u>ቃለ ጉባኤ</u>፦ ሙሉ ቃለ ጉባኤ በስብሰባው ላይ ይያዛል። ከዚህ በፊት የተደረገ ስብሰ ባ ቃለጉባኤ በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ በጽሑፍ ቀርቦ ለአባላት ይታደላል ፣ በዚሁም ይጸድቃል።

ረ. <u>የስብሰባ ሥርአቶች</u>፦ የአባላት ስብሰባ እንደማንኛውም የፓርላማ ስብሰባ ሥርአት ይመራል።

## ቅጽ ፭ የሂሳብ ክፍል

**<u>ክፍል 5-1፦ የሂሳብ መመሪያና አላማ</u>**

የአንድ ድርጅት የሂሳብ አሠራርና አያያዝ ድርጅቱ በማንኛውም ኃላፊነት ያለውን አቋምና ታማኝነት ያንጸባርቃል ብለን እናምናለን። ሉቃስ 16፥11 እንደሚያስተምረን በአመጻ ገንዘብ ካልታመንን በእውነተኛው ገንዘብ (መንፈሳዊ ሀብት) ማን ያምነናል? ስለዚህም በገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ላይ ከታመንን እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ እኛን ለሚሾምበት ነገርና በሚሰጠን መንፈሳዊ ሀብቱና በሰጠን ጸጋ ታማኞች አድረጎ ይቆጥረናል ስለዚህም ይባርከናል (ሉቃስ 16፥10)። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ቤት ገንዘብ በሥርአትና በእምነት ለመጠበቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሂሳብ አሠራር መመሪያዎችና አላማዎች ኃላፊነታችንን ለመወጣት የሚያስችሉን እንዲሆኑና ለአሠራር እንዲረዱ ብለን አዘጋጅተናል።

1. ቤተ ክርስትያንና አገልግሎቷ የእግዚአብሔር ነው። ለማንም ስም ክብር ወይም ማስታወሻ የቆመች ሀውልት አይደለችም። አገልግሎቶቿ በሙሉ የማንንም ሥም አይወክሉም። ንብረቶቿ ከክርስቶስ ኢየሱስ በቀር ለማንም የተሰጡ አይደሉም ። እረኛው፣ ሽማግሌዎቹና እንዲሁም ሌሎቹ አገልጋዮች ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ተወክለው የሚያገለግሉ አገልጋዮች ናቸው።

2. የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን እንድትመሠረት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗል። የክርስቶስ ቤተ ክርስትያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ ለዘላለም ይኖራል ነገር ግን ይህ በዚህች ቤተ ክርስትያን የሚሰጠው አገልግሎት ሊቆም ይችል ይሆናል ። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ የዚህ ድርጅት አገልግሎት ቢዘጋ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት ጋር እንዲሁም ከውጤቱ ጋር እንስማማለን። እስከዚያው ድረስ ግን በእኛ ውስጥ ያለውን ኃይልና ጉልበት በሙሉ በዚህ አገልግሎት ላይ እናሰማራለን።

3. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከምናይባቸው አንዱ መንገድ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስትያን ሥራ በሕዝቡ በኩል በሚልከው የገንዘብ እርዳታ ነው። ስለዚህም በከባድ ወቅቶች ያለውን ሁኔታ ለሕዝቡ እናሳውቃለን። በምንም አይነት አሳፋሪና ግብረገብነት በሌለው አሳዛኝ በሆነ መንገድ ገንዘብን ለቤተ ክርስትያን ለመሰብሰብ አንሞክርም ወይም በውሸት ንግግር ግለሰቦች የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቷቸው ገንዘብ እንዲሰጡ አናደርግም። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ደስ ብሎት እንዳይሰጥ ያደርገዋል (2 ቆሮንቶስ 9፥7)።

4. በቤተ ክርስትያን የሚሰበሰበውን ገንዘብ የእግዚአብሄር ህዝብ ከጉድለቱ የሰጠው እንደሆነ እናውቃለን። መበለቲቱ እነደሰጠችው ሳንቲም (ሉቃስ 21፥ 1-4) እያንዳንዷ ሥጦታ እግዚአብሔርን የሚወድ ሕዝብ በመስዋእትነት የሰጠው መሆኑ እውነት ነው። ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀው የተሰበሰበውን የእግዚአብሔርን ገንዘብ በጥንቃቄና በጥበብ መጠቀም መቻል ነው። እያንዳንዷ ሳንቲም በተቻለ መጠን በወንጌል ሥራ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት እንድትውል ይደረጋል።

5. እግዚአብሔር የሕያው ቃልን ቤተ ክርስትያን የገንዘብ ማስተላለፊያ በማድረግ የተቸገሩ ወገኖችንና ሌሎች የወንጌል አገልግሎቶችን ይረዳል ብለን በሙሉ ልብ እናምናለን። ስለዚህ አስፈላጊ ባልሆኑ የቤተ ክርስትያን ተቀጣሪዎችና ፕሮግራሞች ላይ የገንዘብ ወጪ አናደርግም። ነገር ግን ከገቢያችን ግማሹን (50%) በተለያዩ አገልግሎቶችና የሚሽን ሥራዎች ላይ ለማዋል እንሞክራለን። ይህንንም ስንል እንደ የሰንበት ትምህርት አገልግሎት –ለሕጻናትና ለአዋቂ፣ የእረኛ ደመወዝ፣ የሕንጻ ሥራና የመሳሰሉት ናቸው።

6. ከገቢያችን በላይ ወጪ፣ ባጀት አናደርግም። ሥርአት ያለው ባጀት በማውጣትና በሥርአት በመጠቀም ለፕሮግራሞች የተመደቡትን ወጪዎች አስቀድሞ በማወቅ ገቢና ወጪን ለማስተካከል ጥረት ይደረጋል።

7. መጽሐፍ ቅዱስ በ ምሳሌ 22፥7 ላይ፦ «ተበዳሪ የአበዳሪ ባርያ ነው» በማለት ያስተምረናል። በነጻነ ት እንድናገለግል፣ ተግባራችንን እንድንፈጽም እና እግዚአብሔር እንደመራንም መስጠት እንድንች ል ቤተ ክርስትያንን ከአቅሚ በላይ እዳ ላለማስገባት ጥረት እናደርጋለን። አስፈላጊ ሆኖ እዳ ከተገ ባ በቶሎ ለመክፈልና ከእዳ ለመውጣት ሙሉ ጥረት ይደረጋል።
8. እረኛው ተቀዳሚ እርዳታ ሰብሳቢ ወይም ጠያቂ አይሆንም።

9. ሰይጣን የእግዚአብሔር ሥራ ሲበላሽ፣ ሲቆምና ሲፈርስ ለማየት ከመታገል አያርፍም። በስንፍና፣ በስርቆት፣ በስስት፣ ራስን በመውደድና በተለያየ መንገድ ሊጠቀምብን ይሞክራል። ስለዚህም ለአገልግሎትና ለመሪነት ምርጫ የምናቀርባቸውን ሰዎች በጥንቃቄ፣ በማስተዋልና በጸሎት ከገንዘ ብ ፍቅር ራሳቸውን የጠበቁትን እንመርጣለን(1ጴጥሮስ 5፥2-1፣ ጢሞቴዎስ 3፥3) ።

10. በቂ የሆነ የሂሳብ ምርመራ (ኦዲት) በተወሰነ ወቅት እንደ ሂሳብ አሠራር እንዲደረግ ይሆናል።

11. በማጠቃለያ እኛ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆንን ሁሉ እርሱ በፈቃዱ ባር ኮና ቀድሶ ያቆማት የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋም የእርሱ ናት። እኛ በተሰጠን ዘመን ሁሉ ካለማወቅና ከራስ ወዳድነት በሚመጣ ክፋት እንዳናፈርሳት በፍቅር እናት ልጇን እንደምታ ቅፍ ታቅፈናት እንንዛለን።

## ቅጽ ፮ ሥርአቶችና ልምምዶች

**ክፍል 6-1 ሥርአቶች**

1. የአማኝ ጥምቀት፦ ከኃጢአቱ በንስሀ ተመልሶ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በማመን የሕይወ አቅጣጫውን ለውጦ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድ በእምነትና በሥራ ለ መከተል የወሰነ ሁሉ በውሃ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር መተባበሩን መስክሮ መጠመ ቅ ይችላል።

2. የጌታ እራት፦ የጌታ እራት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን አልፎ በተሰጠበት ጊዜ የመታሰቢያ ሥርአት ሲሆን (1 ቆሮንቶስ 11፥23-26) በዚህም ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ህብረት እንዳለን የምናሳይበት ጊዜ ነው (1 ቆሮንቶስ 10፥ 16-17)። ከኃጢአቱ በንስሀ የተመለሰ ማንኛውም አማኝ ይህንን ሥርአት መካፈል ይችላል (1 ቆሮንቶስ 11፥27-32)

**ክፍል 6-2 ልምምዶች፦**

የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን በኦታዋ የምታደርጋቸው ልምምዶች ከዚህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

1. ሕጻናትን ለጌታ አሳልፎ መስጠት
2. ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መጸለይ
3. ለበሽተኞች መጸለይ
4. የአማኞች ጋብቻን ሥርአት መፈጸም
5. የአማኞችን የቀብር ሥርአት መፈጸም

**ክፍል 6-3፦ የክህነት ሥርአት**

አንድ ሰው ለአንድ አገልግሎት በሽማግሌዎች ቦርድ ከተመረጠና በኋላም ምርጫው በአቀጠቃላይ የአባ ላት ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ በቤተ ክርስትያን ፕሮግራም ላይ የክህነት ሥርአት ይደረጋል። ይህም ሥርአት የሚካነ ውን ሰው በእግዚአብሔር ቃል በመምከር፣ በእረኛው ወይም በሽማግሌ የሚቀርብለትን ጥያቄ እንዲመልስ በማ

ድረግ፣ እጅ በመጫንና በጸሎት ይፈጸማል (የሐዋርያት ሥራ 6፥6፣ 1 ጢሞቴዎስ 4፥14, 5፥22)። ለአገልግሎት የተካኑትን ማበረታታትና መርዳት የቤተ ክርስትያን ኃላፊነት ነው። (1 ተሰሎንቄ 5፥ 12-13፣ ዕብራውያን 13፥17)።

በአጠቃላይ ጉባኤ አባላት ፊት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ለክህነት የቀረበው አገልጋይ በእረኛው ወይም በሽማግሌ ሊጠየቅ ይገባል።

1. የብሉይና አዲስ ኪዳን መጽሐፍት ስህተት የሌለባቸው እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ለእኛም እምነትና መንፈሳዊ ልምምድ ብቸኛ መመሪያ እንደሆኑ ታምናለህ?
2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስትያን ራስ እንደሆነ መዳንም በእርሱ ብቻ እንደሆነ በማመን ለእርሱ ጌትነት ራስህን ለማስገዛት ፈቃደኛ ነህ?
3. ልብህ እንደሚያውቀው የቤተ ክርስትያን ሽማግሌ አገልግሎትን ለእግዚአብሔር ካለህ ፍቅር የተነሳና ለጥሪውም በመታዘዝና የወንጌልን ሥራ ለማሮጥ ካለህ ቅንአትና መነሳሳት ነው የምትቀበለው?
4. ምንም አይነት ፈተና ችግር ቢመጣብህ የቤተ ክርስትያንን ንጽህና፣ ሰላምንና አንድነትንም ለመጠበቅ፣ በወንጌልም እውነት ላይ ጸንተህ ለመቆም ቃል ትገባለህን?
5. በቤትህና በራስህ የግል ኑሮና አካሄድ እንዲሁም በውጭ ባለህ ሕይወት በታማኝነት በመመላለስ ለምታገለግለው የእግዚአብሔር ሕዝብ መልካም ምሳሌ ሆነህ ለመኖር ቃል ትገባለህን?
6. አሁን የቤተ ክርስትያንን የሽምግልና (የዲያቆንነት) አገልግሎትን ኃላፊነት ለመቀበል ዝግጁ ነህን?

የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች፣ የእረኛና የዲያቆናት የክህነት ሥርአት ሲደረግ ጠቅላላ ጉባኤው የቀኝ እጁን በማንሳት ለሚቀጥለው ጥያቄ ቃል ይገባል

መንፈሳዊ መሪነትን ከዚህ ሰው ለመቀበል ዝግጁ ናችሁን?

ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት ነጥቦች ሁሉ የእሺታ መልስ ከተሰጠ በኋላ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎችና ዲያቆናት በተመራጩ ላይ እጃቸውን በመጫን ይጸልያሉ ከዚህም በኋላ ከሽማግሌዎች አንዱ የሚከተለውን ይላል፦

ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ______________________ እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ ሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን የመተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ መሠረት ለሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን የሽምግልና (የእረኝነት) (የዲያቆንነት) አገልግሎት ተከኗል። ይህንንም ዛሬ በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባኤ ፊት አጽድቀናል። ይህን ወንድም/ ይህችን እህት በጌታ ልናከብረውና/ራትና ልናበረታታው/ት ይገባል። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አሜን።

## ቅጽ ፯ እርማት

<u>ክፍል 7-1፦ አሠራር</u>

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በቤተ ክርስትያን ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ላይ እርማት ወይም መስተካከል ይችላል።

1. እርማቶቹ (እርማቱ) በቤተ ክርስትያን ውስጥ ባሉ ቦርዶች፣ ኮሚቴዎች፣ አገልጋዮችና የአገልግሎት ክፍሎች ወይም የሕያው ቃል ቤተ ክርስትያን አባል ከቀረበ

2. **እርማቱ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ከጠቅላላ አባላት ስብሰባ በፊት ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ ለአባላት ተሰጥቶ፣ አለበለዚያም በፖስታ ከ**10 **ቀን በፊት ለአባላት ተልኮ ሲዘጋጅ።**

3. **ከላይ በቁጥር** 2 **በተጠቀሰው ለአባላት በሚሰጠው የእርማት ጹሑፍ የተያያዘ የስብሰባን ቦታና ሰዓት የሚገልጽ ደብዳቤ ሊኖር ይገባል። አለበለዚያም በእሁድ የአምልኮ ስብሰባ በቤተ ክርስትያን ማስታ ወቂያ ለሁለት ሳምንታት መነገር አለበት።**

4. **እርማቱን ለማጽደቅ የአጠቃላይ የጉባኤ አባላት** 3/4 **በላይ መገኘት አለበት በአባላት ከተጠየቀ ድምጽ አሰጣጡ በምስጢር ሊሆን ይችላል**

**<u>ክፍል</u>** <u>7-2</u>**<u>፦ የእምነት አንቀጽ እርማት</u>**

**ምንም አይነት እርማት በቤተ ክርስትያን የእምነት አንቀጽ ላይ ማደረግ አይቻልም።**